## ስለ ትምህርት ቤት ሠላም እና ደህንነት ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ባሉበት መጠለል/shelter-in-place ምንድን ነው?**

ባሉበት መጠለል ማለት በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ንብረት አጠገብ አደጋ ሲኖር የሚከናወን የአደጋ ጊዜ ምላሽ ነው። በትምህርት ቤቱ ዙሪያ ወይም አካባቢ ላይ ስለሚከሰቱ ነገሮች በሰራተኞች አማካይነት የጥንቃቄ ማስገንዘቢያ ይሰጣል። በት/ቤቱ ላይ አደጋ ወይም ስጋት የማይቀር መስሎ ከታየ፣ባሉበት መጠለል "shelter-in-place" ት/ቤቱን በፍጥነት ወደ መቆለፍ እንዲሸጋገር ያዘጋጃል። ድንገተኛ አስቸኳይ የሕክምና ሁኔታዎችንና የደህንነት ሁኔታን ለመቆጣጠርና ወይም የባዮሎጅካል፣ የኬሚካል፣ ወይም የራዲዮሎጅካል መርዛማነት ሁኔታዎች ከተከሰቱ ተማሪዎች ተጋላጭ እንዳይሆኑ በክፍላቸው ውስጥ ባሉበት ለመያዝ "shelter-in-place" ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

**ባሉበት ቦታ በመጠለል ወቅት "shelter-in-place" ምን እርምጃዎችን እንወስዳለን?**

- ሰራተኞች ሁሉንም የውጭ በሮች ይቆልፋሉ እና ይቆጣጠራሉ።
- የክፍል ትምህርት ይቀጥላል።
- ሰራተኞች የትኛውንም የተለየ ሁኔታ ይቆጣጠራሉ/ይከታተላሉ።
- የመተላለፊያ መንገዶች ወይም በኮሪደር ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ የተገደበ ይሆናል።
- ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል አይዘዋወሩም፣ ነገር ግን ባሉበት የመጠለል ሁኔታ እስኪነሳ ድረስ ባሉበት ክፍል ውስጥ ይቆያሉ።
- አስተዳደሩ እንደ አስፈላጊነቱ የደህንነት መረጃዎችን ለማሳወቅ ማስታወቂያዎችን ያስተላልፋል።

**ባሉበት-ቦታ በሚጠለሉበት ወቅት <u>ሰራተኞች</u> ምን እርምጃዎችን ይወስዳሉ?**

- ሰራተኞች ሁሉንም የውጭ በሮች ይቆልፋሉ እና ሁኔታውን ይቆጣጠራሉ።
- የክፍል ትምህርት ይቀጥላል።
- ሰራተኞች የትኛውንም የተለየ ሁኔታ ይቆጣጠራሉ/ይከታተላሉ።
- የመተላለፊያ መንገዶች ወይም በኮሪደር ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ የተገደበ ይሆናል።
- ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል አይዘዋወሩም፣ ነገር ግን ባሉበት የመጠለል ሁኔታ እስኪነሳ ድረስ ባሉበት ክፍል ውስጥ ይቆያሉ።
- አስተዳደሩ እንደ አስፈላጊነቱ የደህንነት መረጃዎችን ለማሳወቅ ማስታወቂያዎችን ያስተላልፋል።

**በያሉበት መጠለል "shelter-in-place" ወቅት <u>ተማሪዎች</u> ምን አይነት እርምጃዎችን ይወስዳሉ?**

- ተማሪዎች በክፍል ትምህርት ይቀጥላሉ።
- ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል አይዘዋወሩም፣ ነገር ግን ባሉበት የመጠለል ሁኔታ "shelter-in-place” እስኪነሳ ድረስ ባሉበት ክፍል ውስጥ ይቆያሉ።

**"lockdown" የእንቅስቃሴ ገደብ ምንድን ነው?**

"lockdown" የእንቅስቃሴ ገደብ ማለት በትምህርት ቤት ግቢ ወይም በአካባቢው ለሕይወት የሚያሰጋ አደጋ ሲከሰት አስቸኳይና ፈጣን ምላሽ መስጠት ነው።

**"lockdown" እንቅስቃሴ በሚገታበት ጊዜ <u>ሰራተኞች</u> ምን እርምጃዎችን ይወስዳሉ?**

- ለማናቸውም ተማሪዎች እና ለሰራተኞች አስጊ አለመሆኑን በመቃኘት ካረጋገጡ በኋላ ከክፍል ውጭ ካሉ ቅርብ ቦታዎች ወዲያውኑ ወደ ክፍላቸው ያስገቧቸዋል።
- በህንፃው ውስጥ ሆነው ነገር ግን ከክፍል ውጪ የሚገኙ ሠራተኞች በቅርባቸው ወደሚያገኙት ለደህንነታቸው ስጋት ወደሌለበት ቦታ መሄድ አለባቸው።
- ከህንፃው ውጭ የሚገኙ ሠራተኞች ቀደም ሲል ወደሚታወቅ ለደህንነታቸው ወደማያሰጋ ቦታ ከህንፃው አጠገብ መራቅና መሄድ አለባቸው (በት/ቤቱ የአስቸኳይ/ድንገተኛ ሁኔታ እቅድ ተለይቶ የታወቀ ሥፍራ ማለት ነው)
- ተማሪዎች ከበር እና ከመስኮቶች አካባቢ ርቀው በክፍል ውስጥ አስተማማኝ ወደሆነ ጥግ ቦታ እንዲሄዱ ይነገራቸዋል።
- በሮች ተቆልፈው ይጠበቃሉ።
- የበር መስኮቶችን ይሸፈናሉ እና መጋረጃዎች ይዘጋሉ።
- መብራቶች ይጠፋሉ።
- ሁሉም የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ድምፅ ይጠፋል።
- ይህን ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የሚቻል ከሆነ ለክትትል እና ለግንኙነት Chromebook/ላፕቶፕ

ይጠቀማሉ።

## ስለ ትምህርት ቤት ሠላም እና ደህንነት ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች

- አላርም/ማንቂያዎችን እና ደወሎችን ችላ ማለት።
- ሌላ መመሪያ እስከሚሰጥ ድረስ መጠበቅ።

**እንቅስቃሴ በተገታበት ወቅት "lockdown" ተማሪዎች ምን አይነት እርምጃዎችን ይወስዳሉ?**

- አስተማሪ ለይቶ በሚያሳይበት ቦታ ከበር እና ከመስኮቶች ርቀው ክፍል ውስጥ ወደ አስተማማኝ ጥግ ይሄዳሉ።
- በህንፃው ውስጥ ሆነው ነገር ግን ከክፍል ወይም ከቢሮ ውጭ ከሆኑ እንቅስቃሴ እንዲገታ ሲገለፅ ተማሪዎች እና ሰራተኞች በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ አስተማማኝ ቦታ መሄድ አለባቸው።
- ከህንፃው ውጭ የሚገኙ ተማሪዎች ከሠራተኞች የሚነገራቸውን መመሪያ በመከተል ለደህንነታቸው እንደማያሰጋ ቀደም ሲል ተለይቶ ወደታወቀ አስተማማኝ ቦታ መሄድ አለባቸው።
- ሁሉም የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ድምፅ ይጠፋል።
- የአስተማሪን ወይም የሰራተኛን መመሪያ ይከተላሉ።
- በፀጥታ ሆነው ተጨማሪ መመሪያዎችን ይጠብቃሉ

**እንደ ወላጅ/አሳዳጊ እንቅስቃሴ በሚገታበት ጊዜ የተማሪን ደህንነት ለመደገፍ ምን ማድረግ እችላለሁ?**

- እርስዎን እናሳውቆት ዘንድ ወቅታዊ የአደጋ ጊዜ መረጃ አስቀድመው መስጠት አለብዎት።
- የትምህርት ቤት ደህንነት እና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነትን በተመለከተ ከልጅዎ ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት ያድርጉ።
- ልጆችዎ ልምምዶችን በቁም ነገር እንዲወስዱ ያበረታቱ እና በደንብ እንዲዘጋጁ ሰራተኞቹ የሚያግዟቸውን ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ይግለጹላቸው።
- የሕግ አስከባሪ እና/ወይም የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎች እስከ ቦታው ድረስ እንደሚመጡ እና የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎችን እንደሚቆጣጠሩ ያስረዷቸው።
- በድንገተኛ ሁኔታ ውስጥ ከልጅዎ ጋር በሚያደርጉት ማንኛውም ግንኙነት ወቅት ተረጋግተው ይቆዩ።
- ግራ መጋባትን ወይም ተጨማሪ የደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል ልጅዎ የትምህርት ቤት ሰራተኞችን መመሪያ እንዲከተል/እንድትከተል ያበረታቱ።
- የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲወስዱ ከጠየቁ፣ እባክዎን ልጅዎ በእርስዎ ቁጥጥር እንዲለቀቅ መታወቂያ ይኑርዎት።

**እንቅስቃሴ በተገደበ ጊዜ እንዴት እና መቼ ነው ኮሙኒኬሽን ማግኘት የምችለው?**

- እንቅስቃሴ ከተገደበ በኋላ በተቻለ ፍጥነት መረጃ ይደርስዎታል።
- ግባችን በተቻለ መጠን 20 ደቂቃ ውስጥ ተከታታይ ወቅታዊ መረጃዎችን መስጠት ነው።
- የመጀመሪያ መረጃ ConnectEd ሲስተም በመጠቀም በስልክ ጥሪ፣ የጽሑፍ መልእክት እና በኢሜል እንዲደርስ ይደረጋል።

**እንቅስቃሴ ከተገደበ " lockdown" በኋላ ኮሙኒኬሽን እንዴት ሊደርሰኝ ይችላል?**

- ስለ ድንገተኛ አደጋ እና ለተማሪዎች/ለወላጆች ያሉትን ሪሶርሶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ የሚሰጥ ተከታታይ ግንኙነት ይደርስዎታል።
- የሁለትዮሽ ግንኙነትን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። እባኮትን እርስዎ ወይም ልጅዎ ስለ ድንገተኛ አደጋ ወይም ስለ ችግር ጊዜ ምላሽ ከባድ ስጋት ካለዎት፣ መረጃ እና መመሪያ ለማግኘት የልጅዎን ትምህርት ቤት በቀጥታ ያነጋግሩ።

**የልጄን ደህንነት ሊነኩ የሚችሉ የድንገተኛ አደጋ ሁኔታዎችን ተከትሎ ምን ዓይነት ድጋፍ ሊደረግ ይችላል?**

- በአእምሮ ጤንነት ሙያ ላይ የተሰማሩ ስፔሻሊስቶች፣ በተለይም የደረሱ ጉዳቶችን በማወቅ እና በመፍታት፣ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር ይሰራሉ።
- ተማሪዎች ማህበራዊ ስሜታዊ ደህንነታቸውን ለመደገፍ ካውንስለሮቻቸውን ሙሉ በሙሉ ማግኘት ይችላሉ።
- መረጃዎችን እየተከታተልን ስናረጋግጥ ለህብረተሰቡ መግለጽ እና ግንኙነት ማድረጋችንን እንቀጥላለን።
- የትምህርት ፈተናዎችና/የቤት ሥራዎችን በመሣሰሉ የአካዳሚክ ስራዎች አስተማሪዎች እንደሁኔታው አመቺነት ያስተካክላሉ።